# የ1991 የሰው ኃይል ጥናት የመጠይቅ ዕርማትና ኮድ

# አሰጣጥ መመሪያ

## (Editing and Coding Manual)

## I. መግቢያ

የሰው ኃይል ስታትስቲክስ መረጃዎች ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የልማት ዕቅዶችን ለ መንደፍ፣ ስለአፈፃፀማቸው ለመከታተልና አስፈላጊ እርምጃዎችን ለመውሰድ መሠረታዊ በመሆናቸው በየወ ቅቱ መረጃዎች በመስኩ እንዲሰበሰቡ ያስፈልጋል። በዚህም መሠረት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን በ መጋቢት 1991 አገር አቀፍ የሰው ኃይል ጥናት በማድረግ መረጃ ሰብስቧል። ጥናቱ ግቡን እንዲመታ አ ስተዋጽኦ ከሚያደርጉት ስራዎች መካከል አንደኛው ከመስክ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በሚገባ አርሞና ኮድ ሰጥቶ ለሚቀጥለው የሥራ ክፍል ማስተላለፍ ነው። ስለሆነም የኮድ አሰጣጥና ዕርማት የማድረግ ተግባር በጥንቃቄ መከናወን ይኖርበታል። በተለይም በዚህ ጥናት ከተካተቱት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጥያቄዎች፣ እነዚህንም ጥያቄዎች እርስ በርስ ለማመሳከር ከሚፈጥረው ውስብስብ አሠራር አኳያ አራሚው ካለ ጥናቱ መረጃ አሰባሰብ በቂ ዕውቀት ሊኖረው ይገባል። በተጨማሪ የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም የአገልግሎት መረጃ ኮድ ሲደረግ በመጠይቁ የተሞሉትን መረጃዎች በጥሞናና በእርጋታ ማየትና መረዳትን ይጠይቃል። ስለሆነም በመጠይቁ እርማትና ኮድ መስጠት ሥራ የሚሳተፉ ሠራተኞች የጥናቱን ውጤት በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ የሥራ ድረሻ የተጣለባቸው መሆኑን አውቀው የእርማትና ኮድ አሰ ጣጡን መመሪያ በደንብ መረዳት ይጠበቅባቸዋል።

## II. አጠቃላይ መመሪያ

1\. የእርማቱና ኮድ አሰጣጡ ሥራ መከናወን ያለበት ለዚሁ በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት መሆን እንዳለበት ማስታወስ ይገባል። አንዳንድ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያልተጠቀሱ ነገሮች ሲያጋ ጥሙ ጥያቄዎቹን ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማቅረብ መፍትሔ እንዲሰጠው ማድረግ ያስፈልጋል ።

2\. ሥራውን ለማከናወን መነሻው በመስክ የተሞላው መረጃ ስለሆነ አስቀድሞ እያንዳንዱ መ ጠይቅ በትክክል ተሞልቶ መምጣቱንና የመጠይቁ ገጾች ሙሉ (5 ገፆች) መሆናቸውን አረጋግጦ መረከብ ያስፈልጋል። ከዚህም ሌላ አንዳንድ በመረጃው አሰባሰብ ጊዜ ያጋጠሙትን ሁኔታዎች የ ሚያብራሩና ከመጠይቁ ጋር ተያይዘው የመጡ አስተያየቶችን በሚገባ መያያዛቸውን ማረጋገጥ ተ ገቢ ነው።

3\. እርማት በሚደረግበትና ኮድ በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉ ሥራው ከሚመለከተው ኃላፊ ካልታ ዘዘ በስተቀር ማንኛውም መረጃ ሰብሳቢው ያስፈረው ነገር መፋቅ/መጥፋት የለበትም። መረጃው

እርማት የሚደረግበት ከሆነ ከሰፈረው መረጃ አጠገብ መረጃው ከተጻፈበት ቀለም በተለየ ቀለም እርማቱ ይደረጋል፡፡

4.

አንዳንድ አስተያየት የተሰጠባቸው መረጃዎች በእርማቱና በኮድ አሰጣጡ ወቅት ልዩ ጥ ንቃቄ የሚሹ ስለሆነ ከመታረሙ በፊት ተቆጣጣሪውን ማሳየት እና እርሱ በሚሰጠው ውሣኔ መ ሠረት መከናወን አለበት፡፡

5. የእርማቱና ኮድ አሰጣጡ ሥራ ጽሕፈቱ በሚነበብ ሁኔታና በንጽህና መሠራት አለበት፡፡

6.

በእያንዳንዱ ዓምድ ኮድ ለማስፈር በተሠሩ ንዑስ አምዶች (ካርድ ኮለሞች) ሁሉ ኮድ የ ተሞላባቸው መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተለይ መረጃው የሚቀነባበረው በኮምፒውተር ስለ ሆነ መረጃውና የጥናቱ ትንተና ዘዴዎች የሚገናኙት በኮድ አማካይነት ብቻ ስለሆነ በከፍተኛ ጥን ቃቄ መሠራት አለበት፡፡

7.

የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ ባልተሞላባቸው መጠይቆች ሁሉ ቤተሰቡ በሚኖርበት የቆ ጠራ ቦታ ከሚኖሩ ሌሎች ቤተሰቦች መጠይቆች በማየት ይሞላል፡፡

8.

ለአንድ ቤተሰብ ከተሞላው የመጠይቆች ጥራዝ የተገነጣጠሉ መጠይቆች ካጋጠሙ የአድ ራሻ መለያውን በመጠቀም በአንድ ላይ ማድረግና መስፋት ያስፈልጋል፡፡

9.

በአምዱ ከቀረቡት ጥያቄዎች ከተዘረዘሩት አማራጮች (ለምሣሌ፡- አዎን/የለም) መረጃ ሰ ብሳቢው በየዓምዱ የሞላው መልስ በየንዑስ ዓምዱ ከተሞሉት ኮዶች ጋር የሚገናዘቡ መሆናቸውን ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡

10.

በአንድ ካርድ ኮለም ንዑስ ዓምድ ከአንድ ቁጥር በላይ መጻፍ ስለሌለበት ይህ በሚያጋጥ ምበት ሁሉ ተገቢው ዕርማት ይደረጋል፡፡

11.

ቁጥሮቹ በካርድ ኮለሞች/ንዑስ ዓምዶች/ በሚጻፉበት ጊዜ ከቀኝ ወደ ግራ መሆን ስለሚ ገባቸው በትክክል መከናወኑን ማየትና ማረም፡፡

12. በዚህ ጥናት መጠይቅ ውስጥ ብዙዎቹ አምዶች ውስጥ «ወደ ዓምድ _______ ይለፉ» የሚሉ ትዕዛዞች ስላሉ ወደተባሉት አምዶች መተላለፋቸውን በጥንቃቄ ማገናዘ ብ ያስፈልጋል፡፡ የይለፍ ሕግ ያላቸው አማራጭ ኮዶች በሙሉ ከጎናቸው የቀስት ምልክት ሲኖራቸ ው ነገር ግን ከጎናቸው ቀስት የሌላቸው ምንም አምድ ሳይዘለልላቸው በቀጥታ ቀጥሎ ያለው አ ምድ የሚጠየቅላቸው ናቸው፡፡ እነዲሁም «ሁሉም ወደ ዓምድ____ይለፍ» የሚል ትዕዛዝ በተሰ ጠ ጊዜ ይህ ትዕዛዝ የተሰጠበትን ዓምድ የተጠየቁ ሰዎች በሙሉ እንዲታለፍ ከተፈለገው ዓምድ በፊት ያሉትን ጥያቄዎች  አይጠየቁም፡፡

## III መጠይቆችን ማረም

## ክፍል 1:- የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ

ከዓምድ 1 እስከ ዓምድ 7 ያለውን የክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ (ከተማ፣ ከፍተኛ) ቀበሌ/ገበሬ ማኀበር ስሞች እና የቆጠራ ቦታ በትክክል መሰጠቱን በማገናዘብ ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ከ ክልል እስከ ቀበሌ/ገበሬ ማህበር ላሉት ዓምዶች ካርድ ኮለሞቹ መስክ ላይ ያልተሞሉ ስለሆነ በ እዝል 1 የቀረበውን የአካባቢ መለያ ኮድ በመጠቀም ካርድ ኮለሞቹን መሙላት ያስፈልጋል፡፡

### ዓምድ 1፡

ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፡- ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል፣ ዞንና ወረዳ ስም በዓምዱ በተሰጠው ቦታ፣ በትክክል መሞላቱ መረጋገጥ አለበት፡፡ በንዑስ ዓምዶቹ ተስማሚው ኮድ ይሞላል፡፡

### ዓምድ 4:-

ከተማ፡- ለከተማው ጥናት የከተማው ስም በተሰጠው ቦታ በትክክል መሞላቱን ማረጋገ ጥ ያስፈልጋል፡፡ ኮዱ ደግሞ በንዑስ ዓምዶቹ ይሞላል፡፡ ለገጠሩ ጥናት ይህ ዓምድ ኮድ 8 ይሞ ላል፡፡

### ዓምድ 5:-

ከፍተኛ/ወረዳ፡- ጥናቱ በከተማ የሚካሄድ ከሆነ የከፍተኛው ስም በዓምዱ በተሰጠው ቦ ታ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ጥናቱ በገጠር የሚካሄድ ከሆነ ኮድ 8 ይሞላል፡፡

### ዓምድ 6:-

ቀበሌ/ገበሬ ማኀበር፡- በከተማ የቀበሌው ስም፣ በገጠር ደግሞ የገበሬ ማኀበሩ ስም በዓ ምዱ በተሰጠው ቦታ መሞላቱን ማረጋገጥ እና በንዑስ ዓምዶቹ የቀበሌው ወይም የገበሬ ማኀበ ሩ ኮድ በትክክል ይሞላል፡፡

### ዓምድ 7:- የቆጠራ ቦታ፡- የቆጠራ ቦታ ኮድ በንዑስ ዓምዶቹ በትክክል መሞላቱን ማጤን ያስፈልጋል፡፡

### ዓምድ 8:-

የተመረጠው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር፡- በአንድ የቆጠራ ቦታ ለጥናቱ የሚመረጡ ቤተሰቦች በጠቅላላ ብዛት 35 ነው፡፡ በዚህ ዓምድ ባሉት ንዑስ ዓምዶች የተሞላው ቁጥር ከ01 - 35 መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ከ35 በላይ የተሞሉ ቁጥሮች ካጋጠሙ ተመርጠው ያልተ ገኙ ቤተሰቦች ሊሆኑ ስለሚችሉ ከ01 - 35 ካሉት ቁጥሮች ውስጥ የጎደለ (የተዘለለ) መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

### ዓምድ 9:-

የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም፡- በዚህ ዓምድ የቤተሰቡ ኃላፊ ሙሉ ስም መፃፉን እንዲሁም በክፍል 2 ዓምድ 11 በመጀመሪያ ተራ ቁጥር ላይ መመዝገቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ባ ይሆን ግን ተቆጣጣሪው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

## <u>ክፍል 2፡</u> <u>ስለቤተሰብ አባላት ዝርዝር መረጃ</u>

## ከዓምድ 10-21 <u>ለሁሉም የቤተሰብ አባላት የሚጠየቁ ጥያቄዎች</u>

**<u>ዓምድ 10</u>፡-** <u>ተራ ቁጥር</u>፡- ይህ ከ01 በመጀመር በተከታታይ ቁጥር የተሰጠበት ስለሆነ ምንም አይነካም፡፡ ሆኖም የቤተሰቡ አባላት ከ11 በላይ በመሆናቸው በተጨማሪነት ጥቅም ላይ የ ዋለ መጠይቅ መሆኑ ከተረጋገጠ እና ተራ ቁጥሮቹ በመስክ ላይ ካልተስተካከሉ አራሚው በተጨማሪ መጠይቅ ላይ «01» ወደ «12»፣ «02» ወደ «13» በመቀየር ማረም ይኖርበታል፡፡

**<u>ዓምድ 11፡-</u>** <u>የቤተሰብ መደበኛ አባላት ሙሉ ስም</u>፡-

የቤተሰቡ አባላት ስም የሰፈረበት ዓምድ ስለሆነ ምንም ዓይነት እርማት አይደረግበትም፡፡

**<u>ዓምድ 12፡-</u>**

<u>ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና</u>፡- በዚህ ዓምድ ሥር ባለው ንዑስ ዓምድ መ ረጃ ሰብሳቢው መሙላት ያለበት የኮድ ቁጥሮች ከ0-8 ያሉ ብቻ ናቸው፡፡ አባላቱ ከቤተሰቡ ኃ ላፊ ጋር ያላቸውን ዝምድና የሚገልጽበት ኮዶች እና የተሰጠው መግለጫና ኮድ ትክክል መሆኑ ን ማረጋገጥ እና የማይዛመድ ከሆነ ኮዱን ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ የኮዶቹ ዝርዝርና መግለጫቸ ው ከጥያቄው ሥር ይገኛል፡፡

**<u>ዓምድ 13፡-</u>**

<u>ጾታ</u>፡- በዚህ ዓምድ ባለው ክፍት ቦታ መታየት ያለባቸው 1 ወይም 2 ብቻ ናቸው፡፡ ስለ ኮዱ ትክክለኛነት በዓምዱ ሥር በተሰጠው ቦታ የሰፈረውን የጾታ መለያ ማየት ያስፈልጋል፡ ፡ ሆኖም መረጃ ሰብሳቢው በስህተት ኮድ ሳይሰጥ ቢቀር ተቆጣጣሪውን በማማከር የግለሰቡን ጾ ታ ከልዩ ልዩ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ መሞላት ይኖርበታል፡፡ ኮድ 9 አይፈቀድም ፆታ ካልተ ገለፈ ስም ታይቶ ይሞላል፡፡ ይህም ካልተቻለ በግምት ይሞላል፡፡

**<u>ዓምድ 14፡-</u>**

<u>ዕድሜ</u>፡- ይህ ዓምድ መስክ ላይ ተሞልቶ የሚመጣ ነው፡፡ ሆኖም በዚህ ዓምድ ባሉት ንዑስ ዓምዶች ከ97 በላይ ቁጥር መታየት የለበትም ከ97 በላይ የሆነ ቁጥር ከታየ 97 ተብሎ መስተካከል ይኖርበታል፡፡ ኮድ 99 አይፈቀድም ዕድሜ ካልተገለፈ ዝምድናና የልጆች ዕድሜ፣ የባ ል ዕድሜ ታይቶ በግምት ይሞላል፡፡ በተጨማሪም የዕድሜ መረጃ ካለተሞላ የቤተሰብ አመዘ ጋገብ ቅደም ተከተልና በዕድሜ ከተገደቡ ዓምዶች ለግለሰቡ የተሞሉ መረጃዎችን በማመሳከር መረጃውን ለመሙላት ይሞክር፡፡ ይኸውም ሲሆን ከተቆጣጣሪው ጋር በመማከር የሚፈፀም ይ ሆናል፡፡

## ዓምድ 15፡- ሃይማኖት፡-

በዚህ ዓምድ ባለው ንዑስ ዓምድ ላይ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከ1-6 ብቻ መሆን አለባቸው:: ከነኚህ ቁጥሮች ውጭ ሌላ ቁጥር ተሞልቶ ከመጣ ሁኔታውን ለተቆጣጣሪው ማሳየትና ማስተካከል ተገቢ ነው:: የሃይማኖት ኮድ ተሞልቶ ካልመጣ፣ ዕድሜአቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ የወላጆቻቸው (የኃላፊው) ሃይማኖት እንደሚከተሉ በማሰብ ተገቢው ኮድ ይሞላል:: ይህም የሚሆነው ከተቆጣጣሪው ጋር በመማከር ነው::

## ዓምድ 16፡- ብሔረሰብ፡-

ለሁሉም የቤተሰብ አባል ከላይ ባለው ክፍት ቦታ ከብሔረሰቡ ስር በሚገኙት ንዑስ ዓምዶች ደግሞ የብሔረሰቡ ኮድ በትክክል መጻፋቸውን ማገናዘብ ያስፈልጋል:: የብሔረሰቦችን ኮድ ዝርዝር ከዚህ መመሪያ ዕዝል 2 ውስጥ ይመልከቱ:: የአንድ ቤተሰብ አባል የብሔረሰብ ዓምድ ካልተሞላ፣ ዕድሜው ከ18 በታች ከሆነ የኃላፊው ብሔረሰብ ይሰጠዋል:: ይህም ሲሆን ከተቆጣጣሪው ጋር መመካከር ያስፈልጋል::

# ከዓምድ 17-21፡- የፍልሰት ሁኔታ

## ዓምድ 17፡- እዚህ ወረዳ ገጠር/ከተማ ውስጥ ያለማቋረጥ ስንት ዓመት ኖረዋል?

ይህ ዓምድ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል አሁን በሚገኝበት ወረዳ ገጠር/ከተማ ውስጥ ያለማቋረጥ ለስንት ዓመት እንደኖረ የሚጠይቅበት ነው:: ለዚህም የተለያዩ አማራጮች ከኮድ 0-8 ከጥያቄው ሥር ተዘርዝረዋል:: ስለሆነም በዚህ ዓምድ ውስጥ በሚገኘው ንዑስ ዓምድ የሚሞላው ቁጥር ከ0-8 ካሉት ቁጥሮች ውጭ መሆን የለበትም:: በተጨማሪም ከተወለዱ ጀምሮ አሁን በሚገኙበት ወረዳ ገጠር/ከተማ ላሉ ማለትም ኮድ 8 ለተሞላላቸው እና ከ5 ዓመት በፊት አሁን ወደ ሚገኙበት ከተማ/ወረዳ ለመጡ (ከኮድ 5-7 ለተሞላላቸው ) ከዓምድ 18-21 ምንም ሳይሞላ በሰረዝ መታለፉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ይህ ዓምድ ሳይሞላ ከመጣ የሚቀጥሉት ዓምዶችን በማየት ወይም ከዕድሜ (በተለይ ለህፃናት) ጋር በማገናዘብ ለመሙላት መሞከር ያስፈልጋል:: ተቆጣጣሪውም ይህን ማየት አለበት::

## ዓምድ 18-21፡- ለፈለሱ (በዓምድ 17 ከኮድ 0-4 ለተሞላላቸው)

## ዓምድ 18፡- እዚህ ወረዳ ገጠር/ከተማ ከመምጣትዎ በፊት የትኛው ክልል ነዋሪ ነበሩ?

በዓምድ 17 ከኮድ 0-4 ውስጥ አንዱ ለተሞላላቸው ቀደም ሲል ይኖሩ የነበሩት የትኛው ክልል እንደነበረ ተጠይቀው የተሞላው ክልል ስም ተመጣጣኙ ኮድ በዓምዱ ሥር በሚገኙት ካርድ ኮለሞች ላይ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የኮዶቹም ዝርዝር ከታች ቀርቧል:: የክልል ስምና ኮድ ሳይሞላ ከመጣ በሚቀጥለው ዓምድ ከተሞላው የዞን ስም በመነሳት መሙላት ይቻል ይሆናል::

## ዓምድ 19፡- እዚህ ወረዳ ገጠር/ከተማ ከመምጣትዎ በፊት የትኛው ዞን ነዋሪ ነበሩ?

በዓምድ 19 ውስጥ የተገለፀው የዞን ስም በዓምድ 17 የተመለከተው ክልል ሥር የሚገኝ መሆኑ መረጋገጥና የዞኑ የተሰጠውም ኮድ ትክክል መሆኑ ይጣራ፡፡ የዞን ስምና ኮዱ አንድ መሆናቸውን ለማመሳከር በዚህ መመሪያ ዕዝል 3 የተሰጡትን የኮድ ዝርዝሮች ይመልከቱ፡፡

## ዓምድ 20፡-

### እዚህ ወረዳ ገጠር/ከተማ ከመምጣትዎ በፊት ቀድሞ ይኖሩበት የነበረው ሥፍራ ከተማ ነበር ወይስ ገጠር?

በዚህ ዓምድ ሥር የሚሰፍረው የከተማ ስም ወይም «ገጠር» የሚለው ቃል ነው፡፡ በካርድ ኮለሙም ውስጥ ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ብቻ ነው መገኘት ያለበት፡፡ ነገር ግን ከላይ ከተገለጸው ውጭ ለከተማ የከተማው ስም መጻፍ ሲኖርበት «ከተማ» ተብሎ ከመጣ ስህተት ሊሆን ስለሚችል ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ ማሳወቅ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ለከተማ ኮድ 1 ለገጠር ደግሞ ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በዞኖች ሥር የሚገኙ ከተሞች ዝርዝር ከዚህ መመሪያ ዕዝል 3 የቀረበ ስለሆነ በዓምዱ የተፃፈው የከተማ ስም ዝርዝር መሠረት ተመሳክሮ ትክክለኛነቱ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## ዓምድ 21፡ የቀድሞ መኖሪያዎን ለመልቀቅ ያበቃዎት ምክንያት ምንድነው?

ይህ ዓምድ በዓምድ 17 ላይ ፈልሰው ማለትም ከኮድ 0-4 ካሉት ኮዶች አንዱ ለተሞላላቸው ግለሰቦች በምን ምክንያት እንደፈለሱ/የቀድሞ መኖሪያቸውን እንደለቀቁ/ ተጠይቆ ምክንያቱ እና ከሥር በሚገኘው ካርድ ኮለም ደግሞ ተስማሚው ኮድ የተ.ሞላበት ዓምድ ነው፡፡ በካርድ ኮለሙም የሚሞሉት ቁጥሮች ከ01-10 ያሉት ብቻ መሆን አለባቸው፡፡ በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለሙ ኮድ 10 ተሞልቶ የሰጡት ምክንያት በዓምዱ ከተመዘገበ ይህን ምክንያት በትኩረት በመመርመር ከጥያቄው ሥር ከ01-09 ከተዘረዘሩት መልሶች ጋር የሚመሳሰል ከሆነ ከካርድ ኮለሙ ኮድ 10ን በመሰረዝ ተቀራራቢውን ኮድ መሙላት ያስፈልጋል፡፡

## ዓምድ 22-23፡- የትምህርት ሁኔታ (ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆኑ ብቻ)

እነኚህ ዓምዶች የሚሞሉት ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ ስለሆነ ከ5 ዓመት በታች ለሆነ ልጅ መረጃ ተሞልቶ ከመጣ ስህተት ስለሆነ ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ በማሳወቅ መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል፡፡ በአንፃሩም ከ5 ዓመት በላይ የሆነ ግለሰብ መረጃ ሳይሞላለት ከመጣ ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት ተገቢውን ኮድ መሙላት ተገቢ ነው፡፡

## ዓምድ 22፡- ማንበብና መጻፍ ይችላሉ ?

ይህ ዓምድ 5 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰቡ አባላት ማንበብና መጻፍ መቻላቸው ተጠይቆ «አዎን» ለመለሱ ኮድ 1 «የለም» ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 የተሞላበት ነው፡፡ ስለዚህ በካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልተው የሚመጡት ቁጥሮች ከ1 ወይም ከ2 ውጭ መሆን የለባቸውም፡፡ ይህ ዓምድ ሳይሞላ ከመጣ በሚቀጥለው ዓምድ (ዓምድ 23) ላይ ከተሞላው መረጃ በመነሳት ማስተካከል ስለሚቻል ኦዲተሩ ለተቆጣጣሪው ማማከር አለበት፡፡

## ዓምድ 23፡ የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ስንተኛ ነው?

በመጀመሪያ በዚህ ዓምድ መረጃ የሚሞላው በዓምድ 22 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ማለትም ማንበብ ና መጻፍ ለሚችሉ ግለሰቦች ብቻ ስለሆነ በዓምድ 22 ኮድ 2 ለተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ምንም ዓይነት መረጃ እንዳልተሞላ ማረጋገጥ ተሞልቶም ከመጣ ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ ጋር በመመ ካከር መረጃውን መሰረዝ እንደሚያስፈልግ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ቀጥሎም ከላይ ባለው ሰፋ ባ ለ ክፍት ቦታ የተጻፈው መረጃ ከሥር በካርድ ኮለሙ ውስጥ ከተፃፈው ኮድ ጋር መጣጣማቸው ን ማገናዘብ ተገቢ ነው፡፡ ለዚህም ከዚህ በታች ያሉትን ኮዶች መመልከት ያስፈልጋል፡፡

## ዓምድ 24-26፡- የሥልጠና ሁኔታ (ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ብቻ)

በነኚህ ዓምዶች መረጃ የሚሞላላቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ግለሰቦች ብቻ ስለሆነ ከ10 ዓመ ት በታች ለሆነው የቤተሰብ አባል መረጃ ተሞልቶ አለመምጣቱን፣ በስህተት ተሞልቶም ከመጣ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አሳይቶ መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል፡፡ በአንፃሩም ከ10 ዓመት በላ ይ ለሆነው ግለሰብ መረጃ ተሞልቶ መምጣት ሲገባው ሳይሞላ ከመጣ ለተቆጣጣሪው ማሳየትና ተገቢው ኮድ እንዲሞላ ማድረግ ያሻል፡፡

## ዓምድ 24፡-

### የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ሥልጠና ወስደውና አጠናቀው የምስክር ወ ረቀት ወይም ከዛ በላይ አግኝተዋል?

በዚህ ዓምድ በሚገኘው ካርድ ኮለም አዎን ለመለሱ ኮድ 1፣ የለም ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 መ ሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ዓምድ የለም መልሰው ኮድ 2 የተሞላላቸው የሚቀጥሉት ዓምዶች ማለትም ዓምድ 25 እና ዓምድ 26 ሳይሞላላቸው በሰረዝ ታልፈው ወደ ዓምድ 27 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ ይህ ዓምድ ሳይሞላ ከመጣ በዓምድ 23 ላይ ከተሞላው መረጃ ጋር በማገናዘብ መሙላት ይቻላል፡፡ ይህም ሲደረግ ተቆጣጣሪው ማየት አለ በት፡፡

## ዓምድ 25፡- የሰለጠኑበት የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ዓይነት ምንድ ነው?

በዓምድ 24 የሰለጠኑበት የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ሥልጠና ወስጀና አጠናቅቂ የምስክር ወ ረቀት ወይም ከዛ በላይ አግኝቼአለሁ ብለው መልሰው ኮድ 1 የተሞላላቸው በዚህ ዓምድ የሰለ ጠኑበት የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ዓይነትና ተገቢው ኮድ በካርድ ኮለሙ መሞላቱን ማረጋገ ጥ ያስፈልጋል፡፡ የሙያ ዓይነቶቹንና ተገቢውን ኮድ ለማገናዘብ ከታች የቀረበውን ዝርዝር ይመ ልከቱ፡፡

## ዓምድ 26፡- የሙያ ሥልጠናውን ከየት አገኙት?

በዓምድ 24 የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ሥልጠና ወስጀና አጠናቅቂ የምስክር ወረቀት ወይም ከዛ በላይ አግኝቼአለሁ ብለው ኮድ 1 የተሞላላቸው በዚህ ዓምድ የሙያ ሥልጠናውን ያገኙበት ተቋም/ድርጅት መሞላቱንና ተገቢው ኮድ ደግሞ ከሥር በሚገኘው ካርድ ኮለም መሞላቱን

ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ኮዶቹም ከተዘረዘሩት 7 አማራጮች ውጭ አለመሆኑን በጽሁፍ የተገለጸ ው ተቋም/ድርጅት ተገቢው ኮድ እንደተሞላለት ማገናዘብ ያስፈልጋል::

## ዓምድ 27:- የጋብቻ ሁኔታ ?

ይህ ዓምድ እንደ «ሥልጠና ሁኔታ» የሚሞላው ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የ ቤተሰቡ አባላት ብቻ ስለሆነ ከ10 ዓመት በታች ለሆኑ ግለሰቦች ሳይሞላ መምጣቱን፣ በስህተት ተሞልቶም ከመጣ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አሳይቶ መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል:: በአንፃሩ ም ከ10 ዓመት በላይ ለሆነው ግለሰብ መረጃ ተሞልቶ መምጣት ሲገባው ሳይሞላ ከመጣ ለተቆ ጣጣሪው ማሳየትና ተገቢው ኮድ እንዲሞላ ማድረግ ተገቢ ነው:: በተጨማሪም በካርድ ኮለም ውስጥ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከኮድ 1-5 ከተዘረዘሩት ውጭ እንዳልሆነ ማየት ያስፈልጋ ል::

ገጽ 2-ክፍል 1:- ከገጽ 1 ክፍል 1 በትክክል መወራረሱን ማገናዘብ ያስፈልጋል::

# ክፍል 3:-

## ያለፉት 12 ወራትና ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ሁኔታ (ዕድሜአ ቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ)

## ዓምድ 11:-

መሉ ስም:- ይህ ዓምድ ከገጽ 1 ዓምድ 11 በቀጥታ የሚወራረስ ነው:: ስለሆም በዚህ ዓምድ የተዘረዘሩት የቤተሰብ አባላት ስም ዝርዝር በገጽ 1 ዓምድ 11 ከተዘረዘሩት ጋር አንድ ዓይነት መሆናቸውን ማመሳከር ያስፈልጋል:: በተለይም የስሞች አመዘጋገብ በሁሉም ገጾች በተ መሳሳይ ቅደም ተከተል መሆኑ መረጋገጥ አለበት:: ይኸም የሚያስፈልገው መረጃ አግድም Key ስለሚደረግ የአንዱ መረጃ ለሌላው እንዳይፃፍ ነው::

## ዓምድ 10:- የመስመር ቁጥር:-

ቀድሞ የተሞላ ስለሆነ አይነካም::

ሆኖም የቤተሰቡ አባላት ከ11 በላይ በመሆናቸው በተጨማሪነት ጥቅ ም ላይ የዋለ መጠይቅ መሆኑ ከተረጋገጠ እና ተራ ቁጥሮቹ በመስክ ላይ ካልተስተካከሉ አራሚው በተጨማሪ መጠይቅ ላይ «01» ወደ «12»፣ «02» ወደ «13» በመቀየር ማረም ይኖርበታል::

# ክፍል 3ሀ:-

## ዓምድ 28-29 ያለፉት 12 ወራት የሥራ ሁኔታ

## ዓምድ 28:-

ባለፉት 12 ወራት ከመጋቢት 90 እስከ የካቲት 91 አብዛኛውን ጊዜ ለክ ፍያ፣ ለትርፍ ወይም ለቤተሰብ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርተዋል?

ለዚህ ጥያቄ እንደ አማራጭ የተሰጡት መልሶች 1. ሠርቻለሁ እና 2.አልሠራሁም ሲሆኑ በዚ ሁ መሠረት በዓምዱ ሥር «ሠርቻለሁ» የሚለው ቃል ከተፃፈ በካርድ ኮለሙ ኮድ «1» መጻፉ ን ወይም ከላይ «አልሠራሁም» ከተፃፈ ከሥር በሚገኘው ካርድ ኮለም ኮድ «2» መጻፉን ማገ ናዘብ ያስፈልጋል።

## ዓምድ 29:- ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ሥራ ያልሠሩበት ምክንያት ምን ነበር?

ይህ ዓምድ የሚሞላው ዓምድ 28 ኮድ «2» ለተሞላላቸው በቻ ሲሆን በዓምዱ ሥር ከ ተዘረዘሩት 9 አማራጭ መልሶች ትክክለኛው ኮድ ብቻ በተሰጠው ካርድ ኮለም መሞላቱን ማረ ጋገጥ ያስፈልጋል። ስለዚህ በካርድ ኮለሙ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከተዘረዘሩት ከ1-9 ኮዱ ች ውጭ መሆን የለባቸውም።

# ክፍል 3ለ:-

## ዓምድ 30-34: ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ሥምሪት ሁኔታ

## ዓምድ 30:-

ይህ ጥያቄ ከዚህ በኃላ ለሚመጡ ጥያቄዎችና ክፍሎች መነሻና መሠረታዊ ጥያቄ ስለሆነ በጥንቃቄ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ስለሆነም ከላይ ከተዘረዘሩት ምርታማ ሥራዎች ቢ ያንስ በአንዱ ለተሰማራ የቤተሰብ አባል «አዎን» የሚለው ኮድ 1 መሞላቱን በአንዳቸውም በአንዳ ም እንኳን ላልተሰማራ «የለም» የሚለው ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ስለዚህ በካ ርድ ኮለሞቹ ውስጥ መታየት የሚገባቸው ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ብቻ መሆን አለባቸው። በተጨ ማሪም «የለም» መልሰው ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣዮቹ ዓምድ 31 እና ዓምድ 32 ሳይሞሉ ወ ደ ዓምድ 33 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ይገባል።

## ዓምድ 31:-

የምሣና የጉዞ ሰዓትን ሳይጨምር ባለፉት 7 ቀናት በ___ ቀን በሥራቸው በሁሉም ስራዎችዎ ለስንት ሰዓት ሰርተዋል?

ይህ ዓምድ ከሌሎቹ ዓምዶች ሰፋ ያለ በእያንዳንዱ ቀን የተሰራ የሥራ ሰዓት መጠን መመዝገቢ ያ ነው። እንደ ዓምድ 30 ሁሉ ይህም ዓምድ መሠረታዊ ነው። ምክንያቱም በሳምንት ውስጥ በሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን ላይ ተመርኩዘን የቤተሰብ አባላትን ሥራ ያላቸው፣ ሥራ አጥ ወይ

ም ከሁለቱም ውጭ ለመከፋፈል ለመክፈል ስለሚረዳን ነው:: ስለዚህ በዚህ ዓምድ ያሉት መረጃ
ዎች በጥንቃቄ መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በመጀመሪያ በእያንዳንዱ ቀን ሥር ተሞ
ልተው የመጡት የሰዓት ብዛቶች «24» መብለጥ የለባቸውም:: ቀን ስም ተሞልተው የመጡት
ቁጥሮች ከ«24» መብለጥ የለባቸውም:: እንዲሁም ክፍልፋይ ሰዓቶች ተጠጋግተው በሙሉ ቁጥ
ር መጻፍ አለባቸው:: በመጨረሻም «የሳምንቱ ድምር» በሚለው ንዑስ አምድ ውስጥ ተሞልቶ
የመጣው ቁጥርና የእያንዳንዱ ቀን ሰዓት ተደምሮ የተገኘው እኩል መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስ
ፈልጋል:: የእያንዳንዱ ቀን ድምር «97» እና ከዛ በላይ ከሆነ «የሳምንቱ ድምር» በሚለው ንዐ
-ስ ዓምድ ሥር መታየት ያለበት ቁጥር «97» ነው:: ይህ ካልሆነ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በ
ማሳየት መረጃውን ማስተካከል ያስፈልጋል:: በተቻለ መጠን በነዚህ ዓምዶች ኮድ 99 እንዳይሰፍ
ር ይፈልጋል:: ምክንያቱም በአንድ ቦታ እንኳን ኮድ 9 ካለ ድምሩ (በታቡሌሽን) ወቅት 99 ስለ
ሚደረግ ነው::

## ዓምድ 32:- <u>በዓምድ 31 ባለፉት 7 ቀናት የሰሩት የስራ ሰዓት ድምር?</u>

ለዚህ ጥያቄ በመጠይቁ ላይ የቀረቡት አማራጮች 2 ሲሆኑ እነዚህም 1. 4 ሰዓትና በላይ፣ 2.
ከ4 ሰዓት በታች የሚሉ ናቸው:: ስለዚህ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ካርድ ኮለም ተሞልቶ የመጣ
ው ቁጥር ኮድ «1» ወይም ኮድ «2» ብቻ መሆን አለበት:: ከዚያም ከ4 ሰዓት በላይ ሰርተው
ኮድ «1» የተሞላላቸው የሚከተሉትን ሁለት አምዶች ማለትም አምድ 33 እና አምድ 34ን ሳ
ይጠየቁ ወደ ዓምድ 35 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

## ዓምድ 33:- <u>ሥራ እያሎት ነበር ባለፉት 7 ቀናት በሥራ ላይ ያልተሰማሩት?</u>

በመጀመሪያ ይህ ዓምድ ላይ መረጃ ተሞልቶ የሚመጣው በዓምድ 32 ኮድ «2» ለተሞላላቸው
ማለትም በአጠቃላይ በሳምንት ውስጥ የሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን ከ4 ሰዓት በታች ለሆነ የቤ
ተሰብ አባላት ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ስለዚህ ከ4 ሰዓት በታች ለሠሩ የቤተሰብ አ
ባላት ሥራ እያላቸው ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በሥራ ላይ ካልተሠማሩ አዎን የሚለው ኮድ «
1» ሲሞላ ነገር ግን ሥራ ሳይኖራቸው ከሆነ የለም የሚለው ኮድ «2» ሊሞላላቸው ይገባል::
በመጨረሻም በዚህ ዓምድ የለም ብለው ኮድ «2» የተሞላላቸው ግለሰቦች እስከ ዓምድ 45 ድረ
ስ ምንም መረጃ ሳይሞላላቸው በቀጥታ ወደ ዓምድ 46 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

## ዓምድ 34:- <u>ባለፉት 7 ቀናት ሥራዎን ያልሠሩበት ምክንያት ምንድነው?</u>

በዚህ ዓምድ መረጃ ተሞልቶ ሊመጣላቸው የሚገባ የቤተሰብ አባላት በዓምድ 33 ኮድ «1» የተ
ሞላላቸው ማለትም ሥራ እያላቸው በሥራ ላይ ያልተሠማሩ ናቸው:: ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ
ከሥራ ሊያስቀሯቸው ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ 6 አማራጭ መልሶች በዚህ ዓምድ ውስጥ ተ
ዘርዝረዋል:: ስለሆነም ምክንያትና በዓምድ የተሰጠው ከሥሩ በሚገኘው ካርድ ኮለም የተሞላ
ው ኮድ ትክክል መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል:: በካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልተው የመጡት ቁ
ጥሮች ከ1-6 ውጭ መሆን የለባቸውም:: በመጨረሻም በዚህ ዓምድ መረጃ የተሞላላቸው ግለሰቦ
ች ሁሉም ወደ ዓምድ 35 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ገጽ 3፡ ክፍል 1፡ ከገጽ 1 ክፍል 1 በትክክል መወራረሱን ማገናዘብ ያስፈልጋል::

ክፍል 4፡ ባለፉት 7 ቀናት በምርታማ ተግባር ለተሰማሩ (ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ)

## ዓምድ 11፡-

ሙሉ ስም፡- ይህ ዓምድ ከገጽ 1 ዓምድ 11 በቀጥታ የሚወራረስ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ዓምድ የተዘረዘሩት የቤተሰብ አባላት ስም ዝርዝር በገጽ 1 ዓምድ 11 ከተዘረዘሩት ጋር አንድ ዓይነት መሆናቸውን ማመሳከር ያስፈልጋል፡፡

## ዓምድ 10፡- <u>የመስመር ቁጥር</u>፡- ቀድሞ የተሞላ ስለሆነ አይገባም፡፡

## ዓምድ 35-45፡ <u>የሥራ ዓይነት፣ ክፍለ ኢኮኖሚ ...፣ የሥራ ለውጥና ከፊል ሠራተኝነት</u>

እነዚህ ዓምዶች የሚሞሉት በጥናቱ ሳምንት በአጠቃላይ የሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን ቢያንስ 4 ሰዓት ለሆነ ማለትም በክፍል 3 ዓምድ 32 ኮድ «1» ለተሞላላቸው ግለሰቦች እና ምንም እንኳ በጥናቱ ሳምንት በአጠቃላይ የሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን ከ4 ሰዓት በታች ቢሆንም ሥራ እያላቸው ላልሠሩ ግለሰቦች ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ በክፍል 3 ዓምድ 32 ወይም ዓምድ 33 ላይ ኮድ 1 የተሞላላቸው በዚህ ክፍል ከዓምድ 35-45 ድረስ መረጃዎች ተሞልተውላቸው መምጣታቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

## ዓምድ 35-41፡ <u>የሥራ ዓይነት፣ ክፍለ ኢኮኖሚ</u>

## ዓምድ 35፡- <u>የዋነኛ ሥራዎ ዓይነት ምንድን ነው?</u>

በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ለነበሩና ሥራ ኖሯቸው በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ያልነበሩ ግለሰቦች በዚህ ዓምድ የዋነኛ ሥራቸው ዓይነት ተሞልቶ መጥቷል፡፡ ለዚህ ዋነኛ የሥራ ዓይነት ተገቢ የሆነው የመለያ ኮድ ከ«የሥራ ዓይነት የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ምደባና ኮድ ዝርዝር» ተብሎ ከተዘጋጀው መጽሐፍ በመውሰድ ይሞላል፡፡ የዋነኛ የሥራ ዓይነቱን ከኮድ ዝርዝሩ መጽሐፍ ውስጥ ማግኘት ካልተቻለ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት ቢቻል ተቀራራቢ የሆነውን የሥራ ዓይነት ኮድ መሙላት ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በመስክ የተሞላው የሥራ ዓይነት ግልጽና በቀላሉ የማይነበብ ለመረዳትም አስቸጋሪ የሆነ ሊያጋጥም ስለሚችል አዲተሩ በእርጋታና በትዕግስት መረጃ ሰብሳቢው የሞላውን መረጃ ማጣራት ይኖርበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሥራ ዓይነት ኮድ ዝርዝሩ ጋር ለማገናኘት ሲሞከር በቅድሚያ የተጠቀሰው የሥራ ዝርዝር በየትኛው ዋና ክፍል እንደሆነ መለየት ከዚያም በዋና ክፍሉ ሥር ከተዘረዘሩት የሥራ ዓይነቶች ለየትኛው እንደሚቀርብ አመዛዝኖ ኮድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ለመወሰን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ተቻኩሎ ኮድ ከማድረግ በመቆጠብና ተቆጣጣሪውን በማማከር ትክክለኛውን ኮድ መስጠት ይገባል፡፡

በኮድ ዝርዝሩ ከተሰጠው የማይገጥም ከተገኘ ከተቆጣጣሪውና ከአሰሪው ክፍል ጋር ተነጋግሮ

አዲስ ኮድ መስጠት ሊያስፈልግ ይችላል፡፡

## ዓምድ 36:- በዋነኝነት የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት ምንድ ነው?

በተመሳሳይ ሁኔታ በጥናቱ ሳምንት በሥራ ላይ ለነበሩና ሥራ ኖሯቸው በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ላልነበሩ ግለሰቦች በዚህ ዓምድ በዋነኝነት የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠ ው አገልግሎት ዓይነት /ኢንዱስትሪ/ ተሞልቶ መጥቷል፡፡ ለዚህ የኢንዱስትሪ ዓይነት ተገቢ የሆ ነው የመለያ ኮድ ከ«የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ኮድ ዝርዝር» ተብሎ የተዘጋጀው መጽሐፍ በመውሰድ ይሞላል፡፡ የኢንዱስትሪ ዓይነቱን ከኮድ ዝርዝሩ መጽ ሐፍ ውስጥ ማግኘት ካልተቻለ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት ቢቻል ተቀራራቢ የሆነውን የኢንዱስትሪ ዓይነት ኮድ መሙላት ያስፈልጋል፡፡ በመስክ ላይ የተሞላው የድርጅቱ ምርት/አገ ልግሎት ሳይሆን የድርጅቱ ስም ወይም ሌላ መግለጫ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህን ጊዜ ከተቆጣጣሪ ው ጋር በመመካከር የድርጅቱ ዋና ምርት/አገልግሎት ምን እንደሆነ ለማወቅ መጣት ያስፈልጋ ል፡፡

## ዓምድ 37:- የዋነኛ ሥራዎ የቅጥር ዓይነት ምንድ ነው?

ለዚህ ዓምድ አራት አማራጭ ኮዶች (ከጥያቄው ሥር) ቀርበዋል፡፡ ስለሆነም ከላይ የቅጥር ዓይነቱ፣ ከሥር በሚገኘው ካርድ ኮለም ደግሞ ተስማሚው ኮድ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨ ማሪም በካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልተው የመጡት ኮዶች ከ1-4 ውጭ መሆን የለባቸውም፡፡

## ዓምድ 38:- የዋነኛ ሥራዎ የቅጥር ሁኔታ ምንድን ነው?

ከላይ በተሰጠው ክፍት ቦታ ተሞልቶ የመጣው የአቀጣጠር ሁኔታ ከሥር በካርድ ኮለሙ ከተሞላ ው ኮድ ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ጥያቄው ሥር የተዘረዘሩት 10 አ ማራጭ መልሶች ከኮድ 01-10 ብቻ ስለሆኑ ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ ሳይሞላ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ከኮድ 01-03 በተጨማሪም ኮድ 09 የተሞላላቸው የቤተሰቡ አባላት እስከ ዓምድ 41 ሳይጠየቁ በቀጥታ ወደ ዓምድ 42 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡

በዓምድ 37 ከኮድ 1-3 የተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ኮድ 06፣ 07፣ 08፣ 09፣ እና 10 እንዳልተሞላላቸ ው ማረጋገጥ ይገባል፡፡

## ዓምድ 39-41:- ክፍለ ኢኮኖሚ

በገጠር መጠይቆች ላይ በግል የግብርና ሥራ ላይ ለተሠማሩ ግለሰቦች እና በገጠርም ሆነ በከተማ በቤት ሠራተኝነት ተቀጥረው ለሚያገለግሉ ተሞልተው የመጡት መረጃዎች በሙሉ ኮድ «2» ማለትም የለም የሚል መልስ እንደተሞላላቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ዓ ምዶች ተሞልተው መምጣት የሚገባቸው ለሁሉም ግለሰቦች ሳይሆን በዓምድ 38 የቅጥር ሁኔታ ዎች ኮድ 03፣ 04፣ 05 ወይም 06 ለሆኑ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ከነዚህ ግለሰቦች ውጭ ለሌሎ ችም መረጃ ተሞለቶ ከመጣ ስህተት ስለሆነ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት መረጃውን መሰረ ዝ ያስፈልጋል፡፡

## ዓምድ 39፡- <u>ድርጅቱ /የሥራ መስኩ የሂሳብ መዝገብ ይይዛል?</u>

በዚህ ዓምድ ለቀረበው ጥያቄ 3 አማራጭ መልሶች ቀርበዋል፡፡ ስለዚህ በካርድ ኮለም ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከኮድ 1፣ 2 ወይም 3 ውጭ አለሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም «አዎን» መልሰው ኮድ 1 የተሞላላቸው ግለሰቦች የሚቀጥሉትን ሁለት ዓምዶች በ« – » ታልፈው ወደ ዓምድ 42 መሻገራቸውን ማገናዘብ ተገቢ ነው፡፡

## ዓምድ 40፡- <u>ደርጅቱ /የሥራ መስኩ ስንት የሥራ ተካፋይ ሠራተኞች አሉት?</u>

በመጀመሪያ በዚህ ዓምድ መረጃ የሚሞላላቸው ግለሰቦች በዓምድ 39 ኮድ 2 ወይም ኮድ 3 የተሞላላቸው ማለትም የሚሠሩበት ደርጅት /ሥራ መስክ የሂሳብ መዝገብ አይዝም ወይም የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለመያዙን አናውቅም ላሉ ግለሰቦቸ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ዓምድ ለነዚህ ግለሰቦች ብቻ መረጃ ተሞልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ዓምድ  ለቀረበው ጥያቄ 2 አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል፡፡ ስለሆነም በካርድ ኮለሙ ተሞልተው የመጡት ኮዶች ኮድ «1» ማለት «10ና በላይ» ወይም ኮድ «2» ማለትም ከ10 በታች የሚሉት ብቻ መሆን አለባቸው፡  በተጨማሪም ከላይ ለተጻፉት ቃላት ከሥር በካርድ ኮለሙ የተሞሉት ኮዶች ተገቢ መሆናቸውን ማገናዘብ ያሻል፡፡ «10ና በላይ» ብለው ኮድ «1» ለተሞላላቸው የሚቀጥለው ዓምድ «41ን» ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 42 መሻገራቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡

## ዓምድ 41፡- <u>ድርጅቱ /የሥራ መስኩ የሥራ ፈቃድ አለው?</u>

ይህ ዓምድ ሊጠየቅላቸው የሚገቡ ግለሰቦች በዓምድ 40 ላይ ኮድ «2» የተሞላላቸው ማለትም ድርጅታቸው /የሥራ መስካቸው ከ10 በታች ሠራተኞች ላሉት ነው፡፡ ለጥያቄውም የቀረቡት አማራጭ መልሶች 3 ብቻ ስለሆኑ ከነዚህ ኮዶች ማለትም ኮድ 1፣ 2 ወይም 3 ውጭ በካርድ ኮለሙ አለመሞላቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡

## ዓምድ 42 – 43፡- <u>የሥራ ለውጥ</u>

## ዓምድ 42፡- <u>ይህ ድርጅት የመጀመሪያዎ ነው?</u>

ይህ ጥያቄ ወደዚህ ክፍል የመጡ ግለሰቦችን ሁሉ ስለሚመለከት ለሁሉም ግለሰቦች መረጃ ተሞልቶ መምጣቱን ማየት ያስፈልጋል፡፡  አሁን የሚሠሩበት ድርጅት የመጀመሪያቸው ለሆኑ ግለሰቦች አዎን በማለታቸው ኮድ «1» መሞላቱን፤ ከዚህ በፊት ሌላ ድርጅት ይሠሩ ለነበሩ ደግሞ የለም በማለታቸው ኮድ «2» ተሞልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ኮድ «1» «ይህ ድርጅት የመጀመሪያዬ ነው ላሉ» ተከታዩ ዓምድ ስለማይመለከታቸው ወደ ዓምድ 44 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ያሻል፡፡

## ዓምድ 43፡- <u>ካለፈው ድርጅት ወይም መሥሪያ ቤት ወይም የሥራ መስክ ለምን ቀየሩ?</u>

በዚህ ዓምድ መረጃ ተሞልቶ ሊመጣ የሚገባው በዓምድ 42 የለም መልሰው ኮድ «2» ለተሞላላ ቸው ማለትም ይህ ድርጅት የመጀመሪያዬ አይደለም ላሉ ግለሰቦ ብቻ ነው፡፡ በዓምድ 42 ኮድ «1» ለተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ላይ መረጃ ተሞልቶላቸው ከመጣ መረጃው ስህተት ስለሆነ ለሚ መለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት መረጃውን መሰረዝ ተገቢ ነው፡፡ ለጥያቄው የቀረቡት አማራጭ መልሶች 7 ብቻ ስለሆኑ በካርድ ኮለም ውስጥ ሊታዩ የሚገባቸው ቁጥሮች ከ1-7 ውጭ መሆን የለባቸውም፡፡ በዚህ ዓምድ ኮድ 7 ተሞልቶ በዓምዱ ክፍት ቦታ ምክንያት ከተመዘገበ ይህን ምክን ያት በትኩረት በመመርመር ከጥያቄው ሥር ከኮድ 1-6 ከተዘረዘሩት መልሶች ጋር የሚመሳሰል ከ ሆነ ኮድ 7ን በመሰረዝ ተቀራራቢውን ኮድ በካርድ ኮለሙ መሙላት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ከላይ በጽሁፍ ለተገለጹት ምክንያቶች ከሥር በካርድ ካለሙ የተሞሉት ኮዶች ተገቢ መሆናቸውን ማገናዘብ ያሻል፡፡

## ዓምድ 44 - 45፡- <u>ከፊል ሠራተኝነት</u>

## ዓምድ 44፡- <u>ባለፈው ሳምንት ይሠሩ ከነበረው ተጨማሪ ሰዓት ለመሥራት አቅምም ፍላጎትም ነበርዎት</u>?

ይህን ዓምድ የሚጠየቀት ወደዚህ ክፍል የመጡ ግለሰሶች ሁሉም ናቸው፡፡ ለጥያቄውም ሁለት አ ማራጭ መልሶች ማለትም አዎን ብለው ለመለሱ ኮድ «1» የለም ላሉ ኮድ «2» በመሙላት ነ ው፡፡ ስለሆነም በካርድ ኮለሙ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከነዚህ ውጭ አለመሆናቸውን ማረጋ ገጥ ይገባል፡፡ የለም መልሰው ኮድ «2» የተሞላላቸው ዓምድ 45 እና ሌሎችንም ተከታይ ዓምዶ ች ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 58 በቀጥታ መተላለፋቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

## ዓምድ 45፡- <u>ተጨማሪውን ሰዓት በምን ዓይነት ሥራ መስማራት ይፈልጉ ነበር</u>?

በዚህ ዓምድ መረጃ ተሞልቶ ሊመጣላቸው የሚገባ ግለሰቦች ዓምድ 44 አዎን ብለው ኮድ «1» የተሞላላቸው ብቻ ናቸው፡ ስለሆነም በዓምድ 44 ኮድ «2» የተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ላይ መ ረጃ ተሞልቶላቸው ከመጣ ስህተት ስለሆነ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል፡፡ የቀረቡት (ከጥያቄው ሥር) አማራጭ መልሶችም 3 ብቻ ስለሆኑ በካርድ ኮለሙ ተ ሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከ1-3 ውጭ መሆን እንደሌለበትና በተጨማሪም በዓምዱ ክፍት ቦታ ለተጻፉት ቃላት ከሥር የተሞሉት ኮዶች ተገቢ መሆናቸውን ማገናዘብ ይገባል፡፡ በመጨረሻም በዚ ህ ዓምድ መረጃ የተሞላላቸው ሁሉም ግለሰቦች ተከታዩን ክፍል ዘለው በቀጥታ ወደ ዓምድ 58 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ገጽ 4፡- ክፍል 1፡- ከገጽ 1 ክፍል 1 ጋር አንድ ዓይነት መሆናቸውን ማገናዘብ ተገቢ ነው፡፡

## ክፍል 5፡- <u>ሥራ አጥነትና የሥራ አጦች ባህሪይ</u>

ዓምድ 10፡- <u>ሙሉ ስም</u>፡- እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ሙሉ ስም ከገጽ 1 ዓምድ 11 በትክክል መወራረሱን ማገናዘብ ይገባል፡፡

ዓምድ 11:- <u>የመሥመር ቁጥር</u>:- ቀድሞ የተሞላ ስለሆነ ምንም አይነካም።

## ዓምድ 46 – 52:- <u>ሥራ አጥነት</u>

### ዓምድ 46:- <u>ባለፉት 3 ወራት ሥራ ለማግኘት ወይም የግል ሥራ ለመጀመር ጥረት አድርገው ነበር?</u>

መጀመሪያ በዚህ ዓምድ ላይ መረጃ የሚሞላላቸው በክፍል 3 ዓምድ 33 ላይ የለም መልሰው ኮድ «2» ለተሞላላቸው ግለሰቦች መሆኑን ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል። ለሌሎች ግለሰቦች ግን ካርድ ኮለሞቹ በሠረዝ «-» ይታለፋሉ።

ለዚህ ዓምድ የቀረቡት አማራጮች አዎን ብለው ለመለሱ ኮድ «1» እና የለም ላሉ ኮድ «2» ስለሆኑ በተገቢው ካርድ ኮለም ከሁለቱ ኮዶች አንደኛው ብቻ መሞላቱን ማረጋገጥ ይገባል። ከዚያም የለም ብለው ኮድ «2» የተሞላላቸው ዓምድ 47ን ተሻግረው ወደ ዓምድ 48 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

### ዓምድ 47:- <u>ሥራ ለማግኘት ወይም ለመጀመር ምን ጥረት አደረጉ?</u>

ይህ ዓምድ የሚሞላው በዓምድ 46 ኮድ «1» ለተሞላላቸው ማለትም ሥራ ለማግኘት ጥረት አድርጌ ነበር ላሉ ግለሰቦች ብቻ ነው። ከዓምዱ ግርጌም 8 አማራጭ መልስ ሊሆኑ የሚችሉ ኮዶች ቀርበዋል። ስለዚህ ከላይ ባለው ክፍት ቦታ ግለሰቡ ያደረጉት ጥረት ከሥር ባለው ካርድ ኮለም ደግሞ ተገቢው ኮድ ተሞልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው። ከዚያም በዚህ ዓምድ ላይ መረጃ የተሞላላቸው ግለሰቦች ሁሉም ወደ ዓምድ 49 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያሻል።

### ዓምድ 48:- <u>ለምንድ ነው ሥራ ለመሥራት ወይም ለማግኘት ጥረት ያላደረጉት?</u>

በመጀመሪያ ይህ ዓምድ የሚሞላላቸው በዓምድ 46 ኮድ 2 ለተሞላላቸው ማለትም ሥራ ለማግኘት ምንም ጥረት ላላደረጉ ግለሰቦች ብቻ ነው። ሥራ ለመሥራት ወይም ለማግኘት ጥረት ያላደረጉበት ምክንያት በዓምዱ ግርጌ ከተዘረዘሩት 11 አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱ በዓምዱ ሥር መሞላቱንና ተገቢው ኮድ ደግሞ በካርድ ኮለሞቹ መሞላቱን ማረጋገጥ ያሻል። የተሰጡት ኮዶች ከ01 – 11 ስለሆኑ በካርድ ኮለሞቹ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከነዚህ ውጭ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል።

### ዓምድ 49:- <u>በሚቀጥለው አንድ ወር ውስጥ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ቢያገኙ ይሠራሉ?</u>

ለዚህ ጥያቄ አዎን ብለው የመለሱ ግለሰቦች ኮድ «1» የለም ብለው ለመለሱ ደግሞ ኮድ «2» እንደተሞላላቸው በተጨማሪም በካርድ ኮለም ውስጥ መታየት የሚገባቸው ቁጥሮችም ከነዚህ ው

ጭ እንዳልሆኑ ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ከዚያም የለም ብለው መልሰው ኮድ «2» የተሞላላቸው ተከታዩን ዓምድ 50ን ዘለው ወደ ዓምድ 51 መሻገራቸውን ማየት ያስፈልጋል::

## ዓምድ 50:- በአቅምዎ ተቀጥረው ሊሠሩት የሚችሉት ሥራ ቢገኝልዎት ወይም በግል ሥራ ለመሠማራት አስፈላጊ ነገሮች ቢሟሉ ሥራ ለመጀመር ዝግጁ ነዎት? ከሆነ የት?

በዚህ ዓምድ ለቀረበው ጥያቄ 6 አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉ መልሶች ከኮድ 1 – 6 የተሰጡ ስለሆነ በካርድ ኮለሙ ተሞልቶ የመጣው ኮድም ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ አለመሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነ ው:: ከዚያም ኮድ 2፣ 3፣ 4፣ 5 ወይም ኮድ 6 የተሞላላቸው ግለሰቦች ተከታዮቹን ሁለት ዓም ዶች ዘለው ወደ ዓምድ 53 መሻገራቸውን ማየት ይገባል:

## ዓምድ 51:- ለምንድ ነው ሥራ ቢያገኙ የማይሠሩት

በዓምድ 50 ላይ ሥራ ቢገኝላቸው ለመሥራት ዝግጁ አይደለሁም ብለው ኮድ 1 የተሞላላቸው ግለሰቦች በሙሉ በዚህ ዓምድ ለምን ሥራ ቢያገኙ እንደማይሠሩ በዓምዱ ሥር ከተዘረዘሩት አማ ራጮች አንዱና ዋነኛው ምክንያት ይሞላል:: ከተዘረዘሩት 8 አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱ በ ዓምዱ ሥር ተጽፎ ተገቢው ኮድ ደግሞ ከሥር ባለው ካርድ ኮለም ላይ መሞላት አለበት:: ስለዚ ህ ካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልቶ የመጣው ቁጥር ከ1-8 ካሉት ውጭ አለመሆኑና ኮዱም ለምክንያ ቱ ተገቢው መሆኑን ማረጋገጥ ያሻል:: ከዚያም ከኮድ 2-8 የተሞላላቸው በሙሉ ወደ ክፍል 6 መተላለፋቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

## ዓምድ 52:- ለምን ከቤት ውስጥ ሥራ ውጭ መሥራት አይፈልጉም?

በዓምድ 51 ላይ ሥራ ባገኝ የማልሠራው ያለክፍያ የቤት ውስጥ ሥራ ላይ ስለተሠማራሁ ነው ላሉ ማለትም ኮድ 1 ለተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ለምን ከቤት ውስጥ ሥራ ውጭ መሥራት እንዳ ልፈለጉ ተጠይቆ ከጥያቄው ሥር ከተዘረዘሩት አማራጭ ኮዶች ውስጥ አንዱና ዋንኛው ተሞል ቶ መጥቷል:: ስለዚህ ከላይ ባለው ክፍት ቦታ ላይ ለተሞላው ምክንያት ተገቢው ኮድ መሞላቱን ና ከሥር ተሞልቶ የመጣው ኮድም ከ1-7 ከተዘረዘሩት ኮዶች ውጭ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈ ልጋል:: በመጨረሻም ይህንን ዓምድ የተጠየቁ ግለሰቦች በሙሉ በዚህ ክፍል ያሉ ተከታይ ጥያቄዎ ች ስለማይመለከቷቸው ሁሉም ወደ ክፍል 6 መተላለፋቸውን በጥንቃቄ ማየት ያስፈልጋል::

## ዓምድ 53:- የሚፈልጉት ሥራ ምን ዓይነት ነው?

በመጀመሪያ ይህ ዓምድ ተሞልቶ የመጣው በዓምድ 50 ላይ ኮድ 2፣ 3፣ 4፣ 5 ወይም ኮድ 6 የተ ሞላላቸው ግለሰቦች ብቻ መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል:: በዓምዱም ተሞልቶ የመጣው መረጃ ከጥ ያቄው ሥር ከተዘረዘሩት 5 አማራጭ መልሶች ውጭ አለመሆኑንና ለመልሱም ተገቢው ኮድ በ ኮድ መሙያ ቦታው ላይ ተሞልቶ መምጣቱን ማየት ያስፈልጋል:: ከዚያም ከኮድ 2-5 የተሞላላ ቸው በሙሉ ተከታዩን ዓምድ ዘለው ወደ ዓምድ 55 መሻገራቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

## ዓምድ 54:- የራስን ድርጅት ለማቋቋም የገጠመዎት /የሚገጥሞት ችግር አለ?

## <u>ካለ ምንድ ነው</u>

ይህ ዓምድ የሚሞላላቸው በዓምድ 53 ላይ ኮድ 1 የተሞላላቸው ማለትም የራሴን ድርጅት ማቋ ቋም እፈልጋለሁ ላሉ ግለሰቦች ብቻ ነው:: የገጠሟቸው ወይም ሊገጥሟቸው ይችላሉ ተብሎ የሚ ገመቱ ችግሮች ከመጠይቁ ግርጌ ከኮድ 00-09 የተዘረዘሩ ስለሆነ ከነዚህ ምክንያቶች ውስጥ አንዳ ኛ ዋንኛው ከላይ ባለው ክፍት ቦታ ላይ ተሞልቶ መምጣቱንና ተገቢው ኮድም ከሥር ባለው ካርድ ኮለም ውስጥ ተሞልቶ መምጣቱን ማገናዘብ ያሻል:: ተሞልተው የመጡት ኮዶች ከ00-09 ካሉት ውጭ አለመሆኑን በጥንቃቄ ማየት ይገባል::

## ዓምድ 55:- <u>ለምን ያህል ወራት ያለሥራ ቆይተዋል?</u>

በዚህ ዓምድ ሥራ አጥ የሆኑ ግለሰቦች በሙሉ ለምን ያህል ወራት ያለ ሥራ እንደቆዩ የሚጠየቁ በት ሲሆን መረጃው በሙሉ ወራት ተሞልቶ መምጣቱን ማየት ተገቢ ነው:: በካርድ ኮለሙ የተ ሞላው ቁጥር ከ97 በላይ ከሆነ ተሠርዞ ኮድ «97» ይደረጋል:: እንዲሁም በመጀመሪያው ንዑስ ዓምድ ምንም ሳይሞላ በሁለተኛው ንዑስ ዓምድ ብቻ ተሞልቶ ከመጣ የመጀመሪያው ንዑስ ዓም ድ ላይ 0 መፃፍ ያስፈልጋል::

## ዓምድ 56:- <u>ከዚህ በፊት በቅጥር ወይም በግል ሥራ ሠርተው ያውቃሉ?</u>

ሥራ አጥ የሆኑ ግለሰቦች ከዚህ በፊት በቅጥር ወይም በግል ሥራ ሠርተው ያወቁ እንደሆነ በዚህ ዓምድ ይጠየቃሉ:: ከዚህ በፊት በቅጥር ወይም በግል ሥራ ተሠማርተው ለሚያውቁ አዎን የ ሚለው ኮድ ፩፣ ወይም በቅጥር ወይም በግል ሥራ ተሠማርተው ለማያውቁ ደግሞ የለም የሚለ ው ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ተሞልተው መምጣት አለባቸው:: ከኮድ 2 ውጪ ተሞልቶ መምጣት የ ለበትም:: በተጨማሪም የለም ብለው መልሰው ኮድ 2 የተሞላላቸው ግለሰቦች ተከታዩን ዓምድ ሳ ይጠየቁ ወደ ክፍል 6 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

## ዓምድ 57:- <u>ለምን የቀድሞ ሥራዎን መሥራት አቆሙ?</u>

ይህን ዓምድ የሚጠየቁት በዓምድ 56 ላይ ኮድ 1 የተሞላላቸው ማለትም ከዚህ በፊት በቅጥር ወይም በግል ሥራ ተሠማርተው የሚያውቁ ግለሰቦች ብቻ ናቸው:: ሥራ ሊያቆሙባቸው ይችላለ ተብሎ የሚገመቱ 11 አማራጮች ከኮድ 01-11 ከመጠይቁ ግረጌ ተዘርዝረዋል:: በመሆኑም የ ቀድሞ ሥራቸውን ያቆሙበት ምክንያት ከላይ ባለው ክፍት ቦታ ተገቢው ኮድ ደግሞ ከሥር ባለ ው ካርድ ኮለም ተሞልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ይገባል:: የተሞሉት ኮዶችም ከኮድ 01-11 ካሉት ውጭ አለመሆናቸውን ማየት ያስፈልጋል:: መጠይቁ ሲዘጋጅ በዚህ ዓምድ ካርድ ኮለም በስህተት ባለ 1 ዲጅት ኮድ እንዲፃፍበት የተደረገ ቢሆንም መረጃ ሰብሳቢዎች ካርድ ኮለሙን ለሁለት ከ ፍለው ኮዶችን እንዲያስገቡ ተደርጓል:: ስለሆነም ኦዲተሩ በቦታ መጥበብ ምክንያት የማይነበቡ ኮ ዶች ካሉ በጥንቃቄ ማረም አለበት::

ገጽ 5:- ክፍል 1:- የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ ከገጽ 1 ክፍል 1 በትክክል መወራረሱን ማገናዘብ ያስፈልጋል::

## ክፍል 6:- ዕድሜአቸው ከ5-14 ዓመት ለሆናቸው ልጆች የሥራ ሁኔታ

በዚህ ክፍል ከዓምድ 58 ጀምሮ ያሉትን ጥያቄዎች የሚመለከቷቸው ዕድሜያቸው ከ5-14 የሆኑ ልጆች ብቻ ስለሆኑ ለነዚህ ልጆች መረጃዎች መሞላታቸውን በአንፃሩም ከዚህ ዕድሜ ገደብ ውጭ ለሆኑ ግለሰቦች መረጃዎች ሳይሞሉ ከዓምድ 58 ጀምሮ እስከ መጨረሻው ዓምድ ድረስ በሠረዝ « - » መታለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በዚህ ክፍል መረጃ የተሞላላቸው ልጆችን ዕድሜ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በገጽ 1 ክፍል 2 ዓምድ 14 ከተሞላው የዕድሜ መረጃ ጋር ማገናዘብ ያ ስፈልጋል::

ዓምድ 1፤ ሙሉ ስም:- ይህ ዓምድ ከገጽ 1 ዓምድ 11 በቀጥታ የሚወራረስ ነው:: ስለሆነም በዚህ ዓምድ የተዘረዘሩትን የቤተሰብ አባላት ስም ዝርዝር በገጽ 1 ዓምድ 11 ከተዘረዘሩት ጋር አንድ ዓይነት መሆናቸውን ማመሳከር ያስፈልጋል::

ዓምድ 10:- የመስመር ቁጥር:- ቀድሞ የተሞላ ስለሆነ አይነካም::

### ዓምድ 58:- በያዝነው የትምህርት ዘመን የመደበኛ ትምህርት እየተማርክ/ሽ ነው?

በያዝነው የትምህርት ዘመን እየተማሩ ላሉ ልጆች አዎን የሚለው ኮድ 1 በትምህርት ላይ ለማ ይገኙ ደግሞ የለም የሚለው ኮድ 2 ተሞልቶ መጥቷል:: ስለሆነም በካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልቶ የመጣው ቁጥር ከኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ውጭ አለመሆኑን ማየት ይገባል:: ከዚያም ኮድ 1 የተ ሞላላቸው ልጆች ተከታዮችን ዓምዶች ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 62 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ያስፈ ልጋል::

### ዓምድ 59 - 61:- በያዝነው የትምህርት ዘመን ለማይማሩ ልጆች ማለትም

### በዓምድ 58 የለም መልሰው ኮድ 2 ለተሞላላቸው ልጆች ብቻ:-

### ዓምድ 59:- ከዚህ ቀደም ተምረህ/ሽ ነበር?

በዓምድ 58 ላይ በያዝነው የትምህርት ዘመን እየተማርኩ አይደለሁም በማለት ኮድ 2 የተሞላላ ቸው ልጆች በዚህ ዓምድ ላይ ከዚህ በፊት ተምረው እንደነበረ ይጠይቃል:: በዓምዱ ሥር ከተሰጠ ጡት 3 አማራጮች ውስጥ አንዱ በዓምዱ ሥር ኮዱ ደግሞ በካርድ ኮለሙ መሞላተላቱን ማረጋገጥ ይገባል:: በመጨረሻም «ምንም ተምሬ አላውቅም» ብለው ኮድ 3 የተሞላላቸው ልጆች ተከታዩ ን ዓምድ ዘለው ወደ ዓምድ 61 መሻገራቸውን ማየት ተገቢ ነው::

### ዓምድ 60:- ትምህርት ያቋረጥክበት/ሽበት ምክንያት ምንድ ነው?

ይህ ዓምድ የሚጠየቅላቸው በዓምድ 59 ኮድ 1 ማለትም «በዚህ ዓመት ጀምሬ አቋረጫለሁ» ወይ ም ኮድ 2 ማለትም «ከዚህ ዓመት በፊት ተምሬ ነበር» ላሉ ልጆች ብቻ ነው:: አማራጭ መልሶቹ ም ከመጠይቁ ግረጌ ከኮድ 01-12 ተዘርዝረዋል:: በመሆኑም በዓምዱ ሥር ትምህርት ያቋረጡበ

ት ምክንያትና ለካርድ ኮለሞቹ ደግሞ ተገቢው ኮድ መሞላቱን ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡ ኮዶቹ ከ0 1-12 ካሉት ውጭ መሆን የለባቸውም፡፡

## ዓምድ 61፡- ባለፉት 7 ቀናት ምን እየሠራህ/ሽ ነበር?

በያዝነው የትምህርት ዘመን በትምህርት ላይ ለማይገኙ ልጆች ባለፉት 7 ቀናት ምን እየሠሩ እንደነበረ ተጠይቆ በዓምዱ ሥር ከተዘረዘሩት 8 አማራጮች ውስጥ አንዱና ዋነኛው በዓምዱ ሥር ኮዱ ደግሞ በካርድ ኮለሙ ተሞልቶ መጥቷል፡፡ ስለሆነም ከላይ ለተጻፈው ጽሁፍ ተገቢው ኮድ መሞላቱን፣ ኮዶችም ከ1-8 ካሉት ውጭ አለመሆናቸውን እንዲሁም ከኮድ 1-6 የተሞላላቸው ወደ ዓምድ 63 ማለፋቸውንና ኮድ 7 ወይም ኮድ 8 የተሞላላቸው ደግሞ ወደ ዓምድ 66 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ዓምድ ከተሞላው መረጃ በዓምድ 30/32 ከተሞሉት መረጃዎች ጋር መጣጣም ስላለባቸው ኤዲተሩ ይህን ዓምድ ሲያርም ዓምድ 30/32ን ማየት አለበት፡፡ በዓምድ 30 ኮድ 2 የተሞላላቸው ወይም በዓምድ 30 ኮድ 1 ቢሞላላቸውም በዓምድ 32 ኮድ 2 የተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ከኮድ 1-6 ተሞልቶላቸው ከሆነ ለተቆጣጣሪው በማሳየት ኮድ 7 በማድረግ ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ በዚህን ጊዜ ከዓምድ 63 እስከ 65 ያሉት ካርድ ኮለሞች « - » ይሆናሉ፡፡

## ዓምድ 62፡- ባለፉት 7 ቀናት ከትምህርትህ/ሽ በተጨማሪ ምን እየሠራህ/ሽ ነበር?

ይህ ዓምድ የሚሞላላቸው በዓምድ 58 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ማለትም በያዝነው የትምህርት ዘመን የመደበኛ ትምህርት በመማር ላይ ላሉ ልጆች ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ልጆች ከትምህርታቸው በተጨማሪ ባለፉት 7 ቀናት ምን እየሠሩ እንደነበር በዚህ ዓምድ ላይ መረጃ ተሞልቶላቸው መጥቷል፡፡ ስለሆነም ለነዚህ ልጆች ከላይ ባለው ክፍት ቦታ ባለፉት 7 ቀናት ምን እየሠሩ እንደነበር ከሥር በሚገኘው ካርድ ኮለም ደግሞ ተገቢ ኮድ መሞላቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ የቀረቡት አማራጭ ኮዶችም 8 ብቻ ስለሆኑ በካርድ ኮለሙ ውስጥ መታየት የሚገባቸው ከ1-8 ካሉት ቁጥሮች ውጭ መሆን የለባቸውም፡፡ በተጨማሪም በዚህ ዓምድ ኮድ 7 ወይም ኮድ 8 የተሞላላቸው ልጆች ተከታዮችን 3 ዓምዶች ሳይጠየቁ በቀጥታ ወደ ዓምድ 66 መሻገራቸውን ማየት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ዓምድ ከተሞላው መረጃ በዓምድ 30/32 ከተሞሉት መረጃዎች ጋር መጣጣም ስላለባቸው ኤዲተሩ ይህን ዓምድ ሲያርም ዓምድ 30/32ን ማየት አለበት፡፡ በዓምድ 30 ኮድ 2 የተሞላላቸው ወይም በዓምድ 30 ኮድ 1 ቢሞላላቸውም በዓምድ 32 ኮድ 2 የተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ከኮድ 1-6 ተሞልቶላቸው ከሆነ ለተቆጣጣሪው በማሳየት ኮድ 7 በማድረግ ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ በዚህን ጊዜ ከዓምድ 63 እስከ 65 ያሉት ካርድ ኮለሞች « - » ይሆናሉ፡፡

## ዓምድ 63፡- ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ መሥራት የጀመርከው/ሽው በስንት ዓመትህ/ሽ ነው (ዕድሜ በሙሉ ዓመት)?

በመጀመሪያ ይህ ዓምድ የሚጠየቅላቸው በዓምድ 61 ወይም በዓምድ 62 ከኮድ 1-6 ካሉት አማራጮች ውስጥ አንዱ ለተሞላላቸው ልጆች (በምርታማ ተግባር ለተሠማሩ) ብቻ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም በካርድ ኮለሞቹ ተመዝግቦ የመጣው ዕድሜ ከልጁ/ልጅቷ ዕድሜ (የማይበልጥ መሆኑን) ማገናዘብ ያሻል፡፡

## ዓምድ 64፡- ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ ለመሥራት ያበቃህ/ሽ ምክንያት ምንድን ነው?

በምርታማ ተግባር ተሰማርተው የነበሩ ልጆች ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ ለመሥራት ያበቃቸው ምክ ንያት በዓምዱ ሥር ተመዝግቦ ተገቢው ኮዱ ደግሞ በካርድ ኮለሙ ተሞልቶ መምጣቱ መረጋገጥ አለበት። ለዚህ ዓምድ የቀረቡት አማራጭ መልሶችም ከመጠይቁ ግርጌ የተዘረዘሩ ሲሆን አማራ ጭ መልሶቹም ከኮድ 1-6 ብቻ ስለሆኑ በካርድ ኮለሙ ተሞልቶ የመጣው ቁጥር ከነዚህ ውጭ አ ለመሆኑን ማረጋገጥ ይገባል። ነገር ግን ኮድ 3 ማለትም «ቤተሰብን ለማገዝ-የቤት ውስጥ ሥራ» የሚለው አማራጭ ምርታማ ሥራ ባለመሆኑ ከመጠይቁ ላይ እንዲሰረዝ ስለተደረገ ይህ መልስ በዚህ ዓምድ ላይ መታየት የለበትም።

## ዓምድ 65:- በሥራህ/ሽ ምክንያት በአካላትህ/ሽ ላይ የደረሰብህ/ሽ ጉዳት/አደጋ አለ? ካለ ደረጃው? _

በዚህ ዓምድ በምርታማ ተግባር ተሰማርተው የነበሩ ልጆች በሥራ ተሠማርተው በነበሩበት ሥራ ምክንያት ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው ከነበረ በዓምዱ «ከባድ» ተብሎ በካርድ ኮለሙ ኮድ «1»፣ መ ጠነኛ ጉዳት ደርሶባቸው ከነበረ ደግሞ «መጠነኛ» ተብሎ ኮድ «2» ወይም ምንም ዓይነት ጉዳ ት ካልደረሰባቸው «አልደረሰብኝም» ተብሎ ኮድ «3» መሞላቱን ማረጋገጥ ይገባል።

## ዓምድ 66:- ወላጅ እናትህ/ሽ በሕይወት አሉ?

ይህ ዓምድ ለሁሉም ልጆች ማለትም ዕድሜያቸው ከ5-14 ለሆኑ በሙሉ የሚጠየቅ ሲሆን በካርድ ኮለሙም መታየት ያለባቸው ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ብቻ ናቸው። ነገር ግን መልስ ሰጪው የወላ ጅ እናቱን/ቷን በሕይወት መኖር አለማወቃቸውን መረጃ ሰብሳቢው በማስታወሻ ጽፎ ከሆነ ኮድ 3 ተደርጎ ይሞላል።

## ዓምድ 67:- ወላጅ አባትህ/ሽ በሕይወት አሉ?

ይህ ዓምድ ለሁሉም ልጆች ማለትም ዕድሜያቸው ከ5-14 ለሆኑ በሙሉ የሚጠየቅ ሲሆን በካርድ ኮለሙም መታየት ያለባቸው ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ብቻ ናቸው። ነገር ግን መልስ ሰጪው የወላ ጅ እናቱን/ቷን በሕይወት መኖር አለማወቃቸውን መረጃ ሰብሳቢው በማስታወሻ ጽፎ ከሆነ ኮድ 3 ተደርጎ ይሞላል።

## ዓምድ 68:- ከማን ጋር ነው የምትኖረው/ሪው?

ዕድሜያቸው ከ5-14 ዓመት የሆናቸው ልጆች በሙሉ ከማን ጋር እንደሚኖሩ ተጠይቀው ከዓምዱ ግርጌ ከተሰጡት አማራጮች በዓምዱ ሥር መልሱ ተመዝግቦ ኮዱ ደግሞ በካርድ ኮለሙ ተሞል ቶ መምጣቱ ማረጋገጥ ይገባዋል። ተሞልቶ የመጣው ኮድ ከተሰጡት 7 አማራጭ መልሶች ውጭ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በዚህ ዓምድ ለተሞላው መረጃ በዓምድ 66 ወይም ዓምድ 67 ከተሞላው መረጃ ጋር መቃረን የለበትም። ለምሳሌ በዓምድ 66 ወላጅ እናቱ/ቷ የሞተችበት/ባ ት ልጅ (ኮድ 2 የተሞላላት በዚህ ዓምድ ኮድ 1 ወይም 3 ሊሞላላት አይችልም።

## ዓምድ 69፡- <u>እናትና አባትህ/ሽ በትዳር ላይ ናቸው?</u>

በዚህ ዓምድ ዕድሜያቸው ከ5-14 የሆነ ልጅ እናትና አባቱ (ሁለቱም በሕይወት ካሉ) በትዳር ላ ይ መሆንና አለመሆናቸው ተጠይቆ ከቀረቡት 3 አማራጭ መልሶች ማለትም አዎን ከሆነ ኮድ 1፣ የለም ከሆነ ኮድ 2 ወይም ልጁ/ልጅቷ ወላጆቹ/ወላጆቿ በትዳር ላይ መሆንና አለመሆናቸውን የ ማያውቅ/የማታቅ ከሆነ ኮድ 3 ተሞልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ፤ በአንፃሩም በዓምድ 66 እና 67 ከወላጆቹ/ከወላጆቿ አንዱ ወይም ሁለቱም በሕይወት ከሌሉ አይመለከታቸውም የሚለው ኮድ 4 መሞላቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡